ግብርና ሚኒስቴር

# የዕጽዋት ዘር ግብይት ማስፈጸሚያ መመሪያ

---

ቁጥር **464/2013**

አዲስ አበባ
የካቲት 2011

መግቢያ

የተሻሻለ የዕጽዋት ዝርያ ዘር ግብይት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው:: በሀገራችን ለበርካታ ዓመታት ሲተገበር የቆየው የዕጽዋት ዘር ግብይት ሥርዓት የተራዘመ የዘር ግብይት ሰንሰለት ያለው፣ የተጠያቂነት ሥርዓት የጎደለው እና መንግስትን ከፍተኛ የሆነ ገንዘብና የሰው ሃይል ሲጠይቅ የቆየ ነው:: በመሆኑም መንግስት የነባሩን የዕጽዋት ዘር ግብይት አሰራር ማነቆዎችን መፍታት የሚያስችል የቀጥታ ዘር ግብይት ሥርዓት በሙከራ ደረጃ ሲተገበር ቆይቷል። የቀጥታ ዘር ግብይት ሥርዓት የዘር አምራች ድርጅቶች ያመረቱትን ዘር ተጠያቂነት ባለው መልኩ በራሳቸው የሽያጭ ወኪል በቀጥታ ለተጠቃሚው በመሸጥ የዕጽዋት ዘርን ከአማራጭ ምንጮች በወቅቱ፣ በሚፈለገው ዓይነት፣ በጥራት፣ በቦታ እና በመጠን እንዲያገኝ በማድረግ የሚያድርን የዘር መጠን ወሳኝ በሚባል መልኩ ቀንሷል።

የቀጥታ ዘር ግብይት ጠቃሚ ተሞክሮዎችን በመቀመርና አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን አሴቶችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የዕጽዋት ዘር ግብይት ተወዳዳሪነት የሰፈነበት እና ገበያ ተኮር እንዲሆን ለማድረግ እንዲቻል በዕጽዋት ዘር አዋጁ 782/2005 እና በደንብ ቁጥር 375/2008 መሰረት ይህን የዕጽዋት ዘር ግብይት መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አውጭው ባለስልጣን

የግብርና ሚኒስቴር ስለ እጽዋት ዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 በአንቀጽ 27/2 መመሪያን ስለማውጣት በተሰጠው ሥልጣንና ስለ እጽዋት ዘር የወጣ ደንብ ቁጥር 375/2008 አንቀጽ 17 የተደነገገውን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ የእጽዋት ዘር ግብይት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር **464/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. ትርጓሜ

በእጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005፣ እና በደንብ ቁጥር 375/2008 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሀረጎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

3.1. "መደበኛ የዕፅዋት ዘር አምራች" ማለት በመደበኛው የዘር ስርአት የተመዘገበን ዘር ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት አግባብነት ባለው ባለስልጣን የተሰጠው ግለሰብ፣ ሕብረት ሥራ ማህበር፣ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ወይም መንግስታዊ ተቋም ነው፡፡

3.2. "አከፋፋይ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብነት ባለው ባለስልጣን የተሰጠው የኢትዮጲያ ዘር ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉና ምንጫቸው የታወቁ የእጽዋት ዝርያ ዘሮችን አምራች ወይም ከውጭ አገር አስመጪ ወይም ከሁለቱም ወይም ከአንዱ ውክልና የወሰደ ሆኖ የእጽዋት ዘር ለሽያጭ ወኪል ወይም ለቸርቻሪ/አግሮዲለር ወይም በግብርና ምርት ውል ለሚያስመርቱ ወይም በሰፋፊ ማሳ ለሚያመርቱ ተጠቃሚዎች በቀጥታ የሚሸጥ ሰው ነው፡፡

3.3. "የሽያጭ ወኪል" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለውና ከእጽዋት ዘር አምራች ወይም ከውጭ አገር አስመጪ ወይም ከአከፋፋይ ጋር በሚገባው ውል መሰረት የእጽዋት ዘር ተረክቦ መያዣው ሳይከፈት ጥራቱ እንደተጠበቀ ለተጠቃሚው በሚወሰንለት ኮሚሽን የሚሸጥ ሰው ነው፡፡

3.4. "ቸርቻሪ/አግሮዲለር" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘና የዕጽዋት ዘርን ከአምራች ወይም ከውጭ አገር አስመጪ እጅ በእጅ ገዝቶ መያዣው ሳይከፈት ጥራቱ እንደተጠበቀ ለተጠቃሚው ራሱ በሚወስነው ዋጋ የሚሸጥ ሰው ነው፡፡

3.5. የዕፅዋት ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል" ማለት የተመዘገበ የዕፅዋት ዘር የሚያመርት አምራች ወይም አከፋፋይ ወይም የሽያጭ ወኪል ወይም ቸርቻሪ/አግሮዲለር የመስክና የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት ጠብቆ አየሰራ መሆኑን የሚቆጣጠርና ማረጋገጫ የሚሰጥ ህጋዊ አካል ነው፡፡

3.6. "አስመጪ" ማለት የእጽዋት ዘርን ከአገር ውጭ ለማስገባት ከግብርና ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ የግልም ሆነ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡

3.7. "የሽያጭ ቦታ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርት ያሟላና የተመዘገበ በአንድ የዘር ወቅት የዕጽዋት ዘር የሚቀርብበትና ተጠቃሚዎችም ቀርበው የሚገዙበት. ነው፡፡

3.8. "አነስተኛ ይዞታ" ማለት የማሳ ስፋቱ ከአሥር ሄ/ር ያልበለጠ ነው፡፡

3.9. "አርሶ/አርብቶ አደር " ማለት በአነስተኛ ይዞታ ሆነ በሰፋፊ መሬት የእርሻን ወይም የእርባታ ሥራ ለመስራት የተሰማራ ሰው ነው፡፡

3.10. "ግብርናን በተመለከተ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል":-ማለት የዕፅዋትና የእንስሳትን ዘር በተመለከተ እንዲመራና እንዲያስተዳድር በክልል መንግሥታት ሥልጣን የተሰጠው ተቋም ነዉ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው የአገሪቱን የዕጽዋት ዘር ጥራት መስፈርት አሟልቶ የዘር ጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በተሰጠው እጽዋት ዘር ላይ ሆኖ፡-

4.1. በመደበኛው የዕጽዋት ዘር ወይም ጥራቱ በተገለጸ ዘር ስርዓት የዝርያ መዝገቦች ውስጥ የተመዘገበና የዘር ጥራት ደረጃ የወጣለት የእፅዋት ሰብል ዘር ላይ፤

4.2. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በተሰጠውና የእጽዋት ዘር በማምረት፣ በማከፋፈል እና በመቸርቸር ተግባር በተሰማራ ሰው ፤

4.3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑሳን አንቀጾች የተገለጸው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው፡-

ሀ/ ማንኛውም ሰው ከእርሻ ምርቱ ጠብቆ በሚይዘውና በሚጠቀምበት ዘር ላይ፤

ለ/ አነስተኛ የማሳ ይዞታ ባላቸው በአርሶ/አደሮች መካከል በሚደረግ ከአርሻ ምርት ተጠብቆ የሚያዝ የዘር ልውውጥ ሆኖ ለንግድ ተግባር የማይውል፣

ሐ/ በደን ዘር እና

መ/ ለምርምር ስራ በሚውል ዘር ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፣

5. **የመመሪያው ዓላማ**

5.1. የዕጽዋት ዘር ግብይት ስርዓቱ በተወዳዳሪነት መርሆዎች ላይ ተሰርቶ ህጋዊ እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲመራ ለማድረግ፤

5.2. የአገሪቱን የዕጽዋት ዘር ግብይት ሥርዓት በአግባቡ በመምራት ዘርን በዓይነት፣ በመጠን፣በጥራት፣ በጊዜ፣ በተፈለገበት ቦታ እና ተወዳዳሪ ዋጋ ለአርሶ/አርብቶአደር ተደራሽ ለማድረግ፤

## **ክፍል ሁለት**

### የዕጽዋት ዝርያን ማስተዋወቅና የምርጥ ዘር ገበያ ፍላጎት ልየታ

6. ሚኒስቴሩና የክልል ቢሮዎች ከሚያከናውኑት ዝርያን የማስተዋወቅ እና ፍላጎት መለየት ተግባር በተጓዳኝ ማንኛውም በዘር ማምረት፣ ማከፋፈልና መቸርቸር የተሰማራ አካል፡-

6.1. የራሱን ዝርያ ዘር ወይም ከሌሎች መንግስታዊ አካላት የሚያገኛቸውን ዝርያዎቸ ዘር የተለያዩ የማስተዋወቅ ዘዴዎችን በመጠቀም ዘሩን ለሚሸጥላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች የማስተዋወቅ ግዴታ ይኖርበታል፤

6.2. በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 6.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሕዝብ ሃብትነት የተመዘገቡ ዝርያዎችን አባዝቶ የሚሸጥ የዕፅዋት ዘር አምራች

ሀ/ የዝርያ ተጠቃሚነት ክፍያ (Royality fee) ያልከፈለ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ ዝርያውን እንዲያመርት ልዩ የተጠቃሚነት መብት (exclusive use right) ከሌለው፣ የማህበራዊ ግዴታውን ከመወጣት አንጻር ከዓመታዊ የተጣራ ትርፉ 0.5 በመቶ የሚሆነውን ለዝርያዎች ማስተዋወቅ እንዲያውል ይደረጋል።

ሐ/ የማህበራዊ አገለግሎት ከመሆኑ አኳያ የማስተዋወቁ ሥራ ገበያ ላይ የገቡና ያልገቡ ዝርያዎችንም ያካትታል።

6.3. የዝርያ ተጠቃሚነት ክፍያ (Royality fee) ለሚከፍል ወይም የህዝብ ሃብት የሆነውን ዝርያ እንዲያመርት ልዩ የተጠቃሚነት መብት (exclusive use right) ያለው ዘር አምራችን የዝርያ ማስተዋወቅ ሥራ ሁለቱንም አስመልክቶ በሚዘጋጀው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

6.4. የዘር አምራቾች የሚያከናውኗቸው አዳዲስ ዝርያን የማስተዋወቅ ተግባር የግብርና ሚኒስቴርና ግብርናን በተመለከተ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል በሚያዘጋጁት ዕቅድ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

7. የእጽዋት ዘር አምራች፣ አምራች ያልሆነ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ዘር ከማምረቱም ሆነ ከማቅረቡ በፊት የዕፅዋት ዘር ገበያ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል።

8. አከፋፋዩ አምራች ከሆነ

8.1. የዕጽዋት ዘር ግብይትን ሥራ በባለቤትነት የሚያከናውን አወቃቀር ሊኖረው ይገባል።

8.2. የዕጽዋት ዘር ከመመረቱ አስቀድሞ የፍላጎት ጥናት ማካሄድና ከሚመለከተው አገራዊ ወይም የክልል የዘር ብዜት ከሚያስተባብር አካል ጋር በትብብር መስራት ይኖርበታል።

8.3. አጠቃላይ የዕጽዋት ዘር አመራረትና ግብይት መከታተል የሚያስችል በዘመናዊ አሰራር የተደገፈ በቀላሉ ከአገራዊ የመረጃ ሥርዓቱ ጋር መያያዝ የሚችል የመረጃ ቋት ሊኖረው ይገባል።

## ክፍል ሦስት

## የእጽዋት ዘር ዋጋ አወሳሰን

9. የእጽዋት ዘር መሸጫ ዋጋን አምራቹ አጠቃላይ ወጪዎችን አገናዝቦ ይወስናል፤

10. አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ የአምራች ወይም የአስመጪ ወኪል ከሆነ የሚሸጥበት ዋጋ ከአምራቹ ጋር በሚገባው ውል መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል፤

11. አምራች ያልሆነ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ (አግሮዲለር) የአምራች ወይም የአስመጪ ወኪል ሆኖ በራሱ ገንዘብ ዘር ገዝቶ የመሸጥ ከሆነ፦

11.1. ገበያን መሰረት አድርጎ ዋጋን ይወስናል፤

11.2. አምራች ያልሆነ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ (አግሮዲለር) ውሳኔ ላይ የደረሰበትን ዝርዝር መሸጫ ዋጋ በየደረጃው ለሚገኝ ግብርናን በተመለከተ ሥልጣን ለተሰጠው የክልል አካል የእጽዋት ዘር ከማቅረቡ በፊት ማሳወቅ አለበት፤

12. ዋጋ ተወስኖ ወደ ሽያጭ ከተገባ በኋላ የዋጋ ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልግ ለውጡ ተግባራዊ ከመደረጉ አስቀድሞ ህጋዊ በሆነ መንገድ ግብርናን በተመለከተ ከክልል ጀምሮ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማሳወቅ ይጠበቃል፤

13. አስፈላጊው የእጽዋት ዘር አቅርቦት እጥረት እና የዋጋ ንረት በየዕፅዋት ዝርያው ዓይነት በሚኖርበት ወቅት የክልል እና የፌደራል መንግስታት የዘርን ዋጋ ለማረጋጋት የሚያስችሉ አማራጭ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ።

## ክፍል አራት

## የአከፋፋይ፣ የሽያጭ ወኪል እና ቸርቻሪ/አግሮዲለር አስተዳደር

14. ማንኛውም የእጽዋት ዘር አከፋፋይ፣ የሽያጭ ወኪል ወይም ቸርቻሪ ለመሆን

14.1. አግባብነት ካለው የዕፅዋት ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል፤

14.2. አግባብነት ካለውና ንግድን በተመለከተ ሥልጣን ከተሰጠው የክልል ተቋም የንግድ ሥራ ፈቃድ ያገኘ መሆን ይኖርበታል፤

15. የሽያጭ ወኪል ለወከለው የዕጽዋት ዘር አምራች ወይም አከፋፋይ ለሚሰጠው አገልግሎት የኮሚሽን አከፋፈል በውል ስምምነታቸው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

16. አንድ የሽያጭ ወኪል፡-

16.1. የተለያዩ የዕጽዋት ዝርያዎች ለሚያቀርቡ አምራቾች ወይም አከፋፋዮች ወኪል ከሆነ ከአንድ በላይ ለሆኑ በወኪልነት ሊያገለግል ይችላል፤

16.2. ወካዩን በብቸኛ ወኪልነት እንዲያገለግው በውል ከተስማሙ የወከለውን አካል ዕጽዋት ዝርያ ዘር ብቻ መሸጥ ይኖርበታል፤

16.3. የዕጽዋት ዘር አምራቾች/ አከፋፋዮች ተመሳሳይ የዕፅዋት ዝርያ የሚያቀርቡ ከሆነ ወኪል መሆን የሚችለው ለአንዱ ብቻ ነው፤

16.4. የሽያጭ ወኪል እጥረት ሲኖር፣ በአንድ ቦታ ለተጠቃሚው አገልግሎት መስጠት ሲፈለግ ወይም አነስተኛ ተጠቃሚ ሲኖር ለተመሳሳይ ዝርያ ለተለያዩ አምራቾች ወይም አከፋፋዮች ወኪል እንዲሆን ሊፈቀድ ይችላል፤

17. አምራች ያልሆነ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ/አግሮዲለር ማንኛውም የዕፅዋት ዝርያ ከሚያመርቱ አምራቾች ወይም አከፋፋዮች ውክልና በመውሰድ በራሱ ገንዘብ ዘር ገዝቶ ማሰራጨት ይችላል።

## ክፍል አምስት

## የዕጽዋት ዘር አቅርቦትና ሥርጭት

18. የዕጽዋት ዘርን ከአምራች ወይም ከአስመጪ እስከ ሽያጭ ቦታ የማቅረብን ተግባር በተመለከተ አምራቹ በራሱ ወይም በአከፋፋይ ወይም በቸርቻሪ/በአግሮዲለር ወይም በሽያጭ ወኪል በውል ስምምነታቸው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤
19. አምራች ያልሆነ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ለመሸጥ በተረከበው የዕጽዋት ዘር አግባብ ያለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ታግ በከረጢቱ ላይ መያያዙን አረጋግጦ መረከብ ይጠበቅበታል፤
20. አምራች ያልሆነ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ተረክቦ በሚያሰራጨው የዕጽዋት ዘር ላይ በአያያዝ ጉድለት ለሚመጣ ማንኛውም የጥራት መጓደል ሃላፊነቱን የመውሰድ ግዴታ አለበት፤
21. በሽያጭ ወኪል አማካይነት ሊደርስ የሚችልን የጥራት መጓደል እና በወኪሉ መጋዝን የሚያድርን ዘር በተመለከተ ወካይ አምራቹ ወይም አከፋፋዩ ከሽያጭ ወኪሉ ጋር በሚገባው ውል መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤
22. የሽያጭ ወኪሉ የዘር ወቅት እስኪጠናቀቅ ድረስ ከሙሉ የሥራ ቀናት በተጨማሪ ቅዳሜ ፣ እሁድና የበዓላት ቀናትን ጨምሮ ለተጠቃሚው አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ በውል ስምምነቱ መካተት ይኖርበታል፤
23. በሰፋፊ እርሻ ላይ የግብርና ሥራን የሚያከናውን አልሚ ባለሃብት (ኢንቨስተር)፡-

 23.1. የሚጠቀምበት ዝርያ እጥረት እንዳለበት ሲታመን ሥልጣን በተሰጠው የክልል አካል በሚወሰነው መሰረት ከአምራቾች በቀጥታ እንዲያገኝ ይደረጋል፤

 *23.2. የዘር እጥረት በሌለበት ወቅት ባለማው እርሻ ልክ ምርጥ ዘር የማግኘት መብት ይኖረዋል፤*

24. አነስተኛ የማሳ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ወይም አርብቶ አደሮች የምርጥ ዘር ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፡-

 24.1. አምራቾች የተሻሻሉ ዝርያዎችን ዘርን በአነስተኛ የዘር እሽግ መጠን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፤

 24.2. እንደ የሰብሉ ዓይነት የአነስተኛ የዘር እሽግ መጠን በሚኒስቴሩ ወይም ሥልጣን በተሰጠው የክልል አካል የሚወስን ይሆናል፤

25. የተሻሻሉ የእጽዋት ዝርያዎች ዘር ተደራሽነት ለማስፋት አምራቾች፣አምራች ያልሆኑ አከፋፋዮችና የሽያጭ ወኪሎች፡-

 25.1. የተለያዩ አዳዲስ የሰብል ዝርያ ዓይነቶች ዘር ለማስተዋወቅ ዘር ሲያቀርቡ፤

 25.2. ተደራሽ ወደ አልሆኑ አዳዲስ አካባቢዎች ምርጥ ዘር ሲያቀርቡና ሲያሰራጩ የማበረታቻ ድጋፎችን ሊያመቻች ይችላል፤



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

26. ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል የሚከናወን የዕጽዋት ዘር አቅርቦትና ሥርጭት ሂደትን በተመለከተ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2010 እና በንግድ ምዝገባና ንግድ አዋጆች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

27. በእጽዋት ዝርያና ዘር አቅርቦትና ሥርጭት ረገድ የመንግስት ሚና በተመለከተ፦

27.1. በመጠንና በዓይነት እጥረት በሚኖርበት ወቅት የፌደራልና የክልል መንግስታት ችግሩን ለመፍታት አስፈላጊውን የመፍትሄ አቅጣጫ ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

27.2. ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን በተመለከተ አምራቾች ወይም አከፋፋዮች ምርጥ ዘር የማያደርሱ ከሆነ ግብርናና ሚኒስቴር ልዩ የድልድል ሥልት ሊከተል ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## መመሪያውን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የዕጽዋት ዘር ግብይት ሥርዓቱ ድጋፍ ሰጪ የመንግስት አካላት ሃለፊነትና ተግባር

### 28. የግብርና ሚኒስቴር

28.1. የዕፅዋት ዘር ግብይትን መመሪያውን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሁለተናዊ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

28.2. ከመነሻ ዘር ማምረት ጀምሮ እስከተመሰከረለት ዘር ብዜት ያለው ሂደት በውል ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ድጋፍ ይሰጣል፤

28.3. በየክልሉ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጽዋት ዘር ግብይት የሚታዩ መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ያስፋፋል፤በአሰራር ረገድ ሃገራዊ የማጣጣም ሥራ ይሰራል፤

28.4. በዕጽዋት ዘር ፍላጎት ልየታ፣ ትንበያ እና ዕቅድ ዝግጅት፣

ሀ/ የእጽዋት ዘር ፍላጎት እንዲፈጠር የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤

ለ/ የዘር አምራቾችን የዝርያ ማስተዋወቅ ሥራ ዕቅድ ዝግጅት ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

ሐ/ የዝርያና ዘር ፍላጎት የልየታና ትንበያ ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

መ/ በየደረጃው ባለው መዋቅር የቀረበለትን የዕጽዋት ዘር ፍላጎት በማጠቃለልና ሌሎች ስትራቴጂክ ጉዳዮችን በማካተት አገራዊ ዕቅድ ያደራጃል፤አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ድጋፍ ይሰጣል፤

28.5. ከክልል ክልል ያለውን የዕጽዋት ዘር ግብይት ማሳለጥ እንዲቻል የመረጃ ልውውጥ ሁኔታን ያመቻቻል፤ድጋፍ ይሰጣል፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

28.6. ከአንድ ክልል በላይ የዕፅዋት ዘር በማከፋፈል ለሚሰማራ አምራች ወይም አከፋፋይ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ህግ፣ ደንብ እና መመሪያን ተከትሎ ያድሳል ወይም ይሰርዛል፡፡

**29. የፌደራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ**

29.1. መመሪያውን ለመተግበር የሚያስችሉ ህብረት ሥራ ነክ ጉዳዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሁለተናዊ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፣

29.2. በየክልሉ በእጽዋት ዘር ግብይት ህብረት ስራ ማህበራትን ይከታተላል፣ይደግፋል፣ መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ያስፋፋል፣ በአሰራር ረገድ ሃገራዊ የማጣጣም ሥራ ይሰራል፣

29.3. ከክልል ክልል ያለውንና በህብረት ሥራ ማህበራት አማካይነት የሚከናወኑ የዕጽዋት ዘር ግብይት ማሳለጥ እንዲቻል የመረጃ ልውውጥ ሁኔታን ያመቻቻል፣ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**30. በክልል ሥልጣን የተሰጠው አካል እስከወረዳ ድረስ የሚገኙ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት የሚመሩ የሥራ ሂደቶች የወል ተግባርና ኃላፊነት፣**

30.1. የዕጽዋት ዘር ግብይት አጠቃላይ ሂደት በዚህ መመሪያና ይህን መመሪያ መሰረት ተደርጎ እንደአስፈላጊነቱ በሚዘጋጁ የየክልሉ የዕጽዋት ዘር ግብይት መመሪያ ይመራል፣ያስተዳድራል፡፡

30.2. የሽያጭ ጣቢያዎች፣ የሽያጭ ወኪሎችን፣ አምራች ያልሆነ አካፋፋዮችንና ቸርቻሪዎችን መረጃ ይሰበስባሉ፣ያጠናቅራሉ፣ ምክረ-ሃሳብ ይሰጣሉ፣

30.3. በራሳቸው አሰራር የለዩትን ፍላጎት ከዘር አምራቾች የዘር ፍላጎት ዳሰሳ ውጤት ጋር በማገናዘብ የመረጃ ማጣጣም ሥራ ያከናውናሉ፣

30.4. በሰሩት የማጣጣም ሥራ መሰረት አምራቾች ያቀረቡት ፍላጎት ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር አንሶ ከተገኘ አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ ሊያግባቡዋቸው ይችላሉ፣

30.5. አምራቾች ከለዩት ፍላጎት በላይ የሆነውን ተጨማሪ ዘር እንዲያመርቱ ከተደረገና ዘሩ ሳይሸጥ ካደረ መፍትሄ ያፈላልጋሉ፡፡

30.6. ከአምራቾች ጋር ስምምነት ላይ በተደረሰው ፍላጎት መሰረት የተቀናጀ ዘር ማምረትና የአቅርቦት እቅድ ያዘጋጃሉ፣

30.7. በተዘጋጀው ዕቅድ መሰረት ለሁሉም አምራቾች መነሻ ዘር እንዲቀርብ ያመቻቻሉ፣

30.8. የሽያጭ ወኪሎች ወይም ቸርቻሪ/አግሮዲለር የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ መስፈርቶችን አስቀድመው እንዲያሟሉ ክትትል ያደርጋሉ፣

30.9. የአቅም ግንባታ ስልጠና ድጋፍ ለዘር አምራቾች፣ለወኪሎችና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ይሰጣሉ፣

30.10. ወቅታዊ የዘር ገበያ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ያደርጋሉ፣

30.11.መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራሉ፤ ተደራሽ እንዲሆኑም ያደርጋሉ፤

30.12.በዚህ መመሪያ መሰረት የዕጽዋት ዘር ግብይቱ በፍላጎትና አቅርቦት መርሆዎች መሰረት እየተመራ መሆኑን ለማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋሉ።

## 31. የዕጽዋት ዘርና ሌሎች ግብርና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር አግባብነት ያለው የክልል ባለስልጣን

31.1. በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ አምራቹ፣አከፋፋዩ እና የሽያጭ ወኪሉ ስለ ዕጽዋት ዘር የወጣን አዋጅ ፣ደንቦችና መመሪያዎች ተከትለው እየሰሩ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

31.2. በዘር ጥራት ቁጥጥር ዙርያ ያሉትን የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮችን ለሽያጭ ወኪሎች፣ ለአከፋፋዮች፣ ለቸርቻሪዎች እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ስልጠና ይሰጣል፤

31.3. በክልሉ ውስጥ ዘር ለሚያከፋፍል፣ ለሚቸረችር እና በዘር ሽያጭ ወኪልነት ለተሰማራ አካል የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤ይከታተላል፣ ይደግፋል፤ ያድሳል፤ይሰርዛል፤

31.4. ለዘር ግብይት የቀረበው ዘር የብቃት ማረጋገጫ ስርተፊኬት ባገኘ አምራች የተመረተ እና የዘር ጥራት ስርተፊኬት የተሰጠው መሆኑን ያረጋግጣል፤

31.5. የዘር ጥራት ቁጥጥር ተካሂዶ የጥራት ማረጋገጫ ካገኘ በኋላ በዘር ግብይት ጣቢያዎች የገባ ዘር ጥራቱን ጠብቆ እየተሰራጨ መሆኑን ይከታተላል፤ያረጋግጣል።

31.6. እንደአስፈላጊነቱም በዘር ሽያጭ ከሚሰራጨው ዘር ናሙና ወስዶ የድህረ ቁጥጥር ጥራት ሙከራ ያካሂዳል፤ በመስክ ከአርሶአደር ማሳ ከተሰበሰበው ግብረ-መልስ ጋር በማገናዘብ ውሳኔ ይሰጣል፤

31.7. በዘር ሥርጭት ወቅት በተሽከርካሪ እየተጓዘ ባለዘር ላይ ድንገተኛ የጥራት ቁጥጥር ሥራ ያካሂዳል፤ችግር እንዳለ ሲያረጋገጥ ከፍትህ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

31.8. በዘር ግብይት የሚሳተፍ የሽያጭ ወኪል፣ ቸርቻሪ፣ አከፋፋይ የሸጠውን ዘር መሰረት በማድረግ የተሰራጨውን ከረጢት መለያ ቁጥር በመመዝገብ መረጃ (በአምራች፣ በመጠን፣በዝርያ፣ በተጠቃሚ አርሶአደር/አርብቶአደር) መያዙን ያረጋግጣል፤

31.9. ምርጥ ዘር በሚሸጥበት ወቅት የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል የሰጠውን የዘር ጥራት ውጤት በሻጭ እጅ መገኘቱንና መረጃ ለተጠቃሚው ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጣል፤

31.10.የእጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና ከዘር ጥራት ቁጥጥር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ደንቦችና መመሪያዎች ተላልፎ የሚገኝን ሰው በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የህግ ክፍል አማካይነት ለሚመለከተው የፍትህ አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤

31.11.ከፌደራል መንግስት እስከአሁን በወጡ አዋጅ፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ያልተገለጹ ግን ይህን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ እንቅፋት ሊሆኑ በሚችሉ ጉዳዮች ተጨማሪ

ማብራሪያዎችን በማካተት እና የክልሉን ባለድርሻ አካላት በማስተባበር መመሪያውን ማጎልበት ይችላል፤

31.12. አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በዚህ የዘር ግብይት መመሪያ በማካተት ሂደት ግን የፌደራሉ መንግስት ስለ ዕጽዋት ዘር ካወጣቸው ህጎች ጋር በማይቃረን መልኩ መከናወን ይኖርበታል፡፡

## 32. የክልሉ የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች እና በተዋረድ የሚገኙ ጽ/ቤቶች፡-

32.1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት በዚህ መመሪያ መሰረት የዕጽዋት ዘር ግብይት ሂደቱን እንዲያከናውኑ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፤ ተግባራቸውን እያከናወኑ ስለመሆኑ በጥናት ይለያል፤ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

32.2. መመሪያው የህግ ክፍተቶች አሉት ብሎ ባመነ ጊዜ ግብርናን በሚመለከት አግባብ ካለው የክልል ባስልጣን ጋር በመሆን በጥናት ያረጋግጣል፣ ለፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ያሳውቃል፣ መሻሻል ሲያስፈልግ ለግብርና ሚኒስቴር ጥያቄ ያቀርባል፤

32.3. ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዚህ መመሪያ መሠረት ተግባሮቻቸውን እንዳያከናውኑ የሚያደርጉዋቸው ማነቆዎችን በመለየት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፤

32.4. በሽያጭ ወኪልነት ወይም ቸርቻሪነት ወይም አከፋፋነት ወደ ተመዘገቡ የህ/ሥ/ማህበራት የገባው ዘር በአግባቡ እንዲሠራጭ ድጋፍ ይሰጣል፤

32.5. ህብረት ሥራ ማህበራት የዕጽዋት ዘርን በማከፋፈልና በመቸርቸር እንዲሰማሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አግባብ ካለው የክልል ባለሥልጣን እንዲያኙ ያበረታታል፤ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 33. የአርሶ አደሩ/ከፊል አርብቶ አደር ግዴታ

33.1. ማንኛውም አርሶ/አርብቶ አደር የዕፅዋት ዘር ከመግዛቱ በፊት የዘር ሽየጭ ወኪል ወይም ቸርቻሪ ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ መሆኑን፣ የሚሸጠውም ዘር የጥራት ማረጋገጫ ያገኘ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለ ቅሬታ አቀራረብ

34. በአከፋፈይና በወኪል፣በአከፋፋይና ቸርቻሪ/አግሮዲለር መካከል የሚከሰት ቅሬታ አፈታት

34.1. በአከፋፈይና በወኪል ቅሬታ ሲፈጠር ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት ቅሬታውን በውላቸው መሰረት እንዲፈቱ ይበረታታሉ፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

34.2. በገቡት ውል መሰረት ቅሬታውን መፍታት ካልቻሉ በውላቸው ውስጥ ለተካተተ ሶስተኛ ወገን ያቀርባሉ፤ ይደራደራሉ፤መግባባትም ላይ እንዲደርሱ ጥረት ያደረጋሉ፤

34.3. በድርድር በተደረሰው ውሳኔ ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለሚመለከተው የፍትህ አካል በ30 ቀናት ውስጥ አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት ይችላል።

35. አርሶአደሩ ወይም ከፊል አርብቶአደሩ በዘር ግብይት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ቅሬታ በሚኖረው ጊዜ ቅሬታውን ለሚመለከተው የወረዳ የግብርና ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል፤

36. አርሶ/አርብቶ አደሮች በዘር ጥራት ጉድለት የተነሳ ቅሬታ በሚኖራቸው ጊዜ የአፈታት ሂደት፡-

36.1. በመጀመሪያ ደረጃ ቅሬታቸውን ለሽያጭ ወኪሉና ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ወዲያውኑ ያቀርባሉ፤

36.2. በቀረበው ቅሬታ መሰረት ጽ/ቤቱ በራሱ ባለሙዎች ቅሬታው በአምስት ቀን ውስጥ እንዲጣራ ያደረጋል፤

36.3. የጥራት ጉድለቱ መንሲኤ በወረዳ ደረጃ የማይፈታ ከሆነ ጽ/ቤቱ የባለሙዎቹ ሪፖርት በደረሰው በ3 ቀን ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው የክልል የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ያቀርባል፤

36.4. የክልል አግባብ ያለው ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሪፖርቱ ከወረዳ እንደቀረበለት አጣሪ አካል ከአምራቹ ተወካይ ጋር በማቀናጀት በሁለት ቀናት ውስጥ ቅሬታ ወደቀረበበት ወረዳ ይልካል፤

36.5. በወረዳ ደረጃ የተነሳው ቅሬታ እንዲፈታ የተላከው የክልል አግባብ ያለው ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ቡድን፡-

ሀ/ ቅሬታው ያለ ዘር ናሙና ፍተሻ ሊፈታ የሚችል ከሆነ በአምስት ቀናት ውስጥ ለቀረበው ቅሬታ በወረዳ ደረጃ መፍትሄ ይሰጣል፤

ለ/ ቅሬታው ተጨማሪ የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ የሚጠይቅ ከሆነ ላቦራቶሪዎች ናሙና ወስደው እንዲፈትሹ እና እንደ የሰብሉ የብቅለት ጊዜ ከ7 እስከ 21 ባሉት ቀናት ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

ሐ/ አርሶ/አርብቶ አደሮች አግባብ ባለው ባለስልጣን የተሰጠው ውሳኔ ካለረካቸው ስለ ዕጽዋት ዘር በወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 መሠረት ቅሬታቸውን በ 30 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ማቅረብ ይችላሉ።

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

37. ቅሬታና ቅጣት

ቅሬታና ቅጣትን በተመለከተም ግብርና ሚኒስቴርና ግብዓት ጥራት እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው የክልል አካል ባወጧቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

38. የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የሚመለከተው ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

39. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

የዕፅዋት ዘር ግብይትን አስመልክቶ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያና የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ አይሆንም።

40. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ **ከመጋቢት 2 ቀን 2011ዓ.ም** ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ዑመር ሁሴን

ግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር